በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

# ዜና ቤተ ክርስቲያን

## ዘኢትዮጵያ

### ፳፭ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ጵጵስና

### የብር ኢዮቤልዩ



የመጀመሪያዎቹ ፭ቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት

www.ethiopianortodox.org

ይህ መጽሔት በኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ በስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ ዋና መምሪያ በመጽሔትና በጋዜጣ ማዘጋጃ ክፍል ለ፳፭ኛው የጵጵስና የብር ኢዮቤልዩ በተለይ ተዘጋጀ

ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ፡ ም.

www.ethiopianortodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን፡ ነ፡ ፡ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianortodox.org



ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ

www.ethiopianortodox.org





ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianortodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ

www.ethiopianortodox.org

ረታና ቤተሰቡ
ቤተ መጻሕፍት

# ከዕጨጌነት እስከ ጵጵስና

«የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ጳጳሳትን አይሹሙ» በሚለውና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የኒቅያ ጥቅስ ነው ብላ ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አባቶች ጳጳሳትን ላለመሾም በተጠቀመችበት የፈጠራ ጥቅስ የኢትዮጵያና የእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ሁለቱ ከ፩ሺ፮፻ ዘመናት በላይ በጥያቄና በመልስ ሲወዛገቡ መኖራቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስታውሰዋል ።

በዚሁ መሠረት በ፲፱፻፵፩ ዓ ም ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት አድባራትና ገዳማት የተውጣጡ ፸፪ ሊቃውንትና ፳፬ መምህራን በድምሩ ፺፮ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና የቤተ መንግሥት መልእክተኞች በኅዳር ፱ ቀን እሁድና በኅዳር ፲፫ ቀን ሐሙስ ዳግመኛም በኅዳር ፲፯ ቀን ሰኞ በቅድስት ሥላሴ ገዳም ተሰብስበው በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርገው የተቀደሰው ዐቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ከተከፈተ በኋላ ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚመተ ጵጵስና ጉዳይ የተነጋገሩበትን ዝርዝር ሐሳብና የሰጡትን ውሳኔ ታሪክን ለማስታወስ ያህል ከዚህ ቀጥሎ መመልከት ይገባል ።

## የ፵፩ቱ ሊቃውንት ዐቢይ ጉባኤና ውሳኔ

፩ኛ/ ጉባኤው የተሰበሰበበት የነገሩ ዋነኛው አርእስት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት መሆን የሚገባው ኢትዮጵያዊ ወይም ግብፃዊ እንደሆነ ለመለየትና መንፈሳዊ ውሳኔ ለመስጠት ነው ። በዚሁ ጉዳይ ምክንያት በየጊዜው የተጻፉትን ጉባዔው ስለመረመረ ፤

ሀ/ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ከ፭ ጥያቄዎች ጋራ የጻፈውንና የእስክንድርያ ፓትርያርክ የላከውን ደብዳቤ ።

ለ/ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አንድ ዓመት ያህል ቆይተው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ካቀረባቸው ጥያቄዎች ዓይነተኞቹን ሁለቱን ጉዳዮች አለመቀበላቸውን እያስረዱ ትእዛዝ ብለው በ፲፱፻፵፪ ዓ ም ሰኔ ፱ ቀን የጻፉትንና ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ የላኩትን ቃል ፤

ሐ/ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በ፲፱፻፵፪ ዓ ም ሐምሌ ፯ ቀን ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ያቀረበውን የውሳኔ ማስታወቂያ ፤

፪ኛ/ ጉባኤው ከመረመራቸው ነገሮች አንዳንዶቹን ከዚህ ማንሳት አስፈላጊ ነው ።

ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የጠየቀችው ሊቀ ጳጳሳትዋ ከተወላጆችዋ መካከል በሊቃውንቶችዋ እየተመረጠ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ባርከው እንዲሾሙላት እንዲሁም በበታቹ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም መብት ያለው እንዲሆን ነው ።

ለ/ የግብፅ ቤተክርስቲያን ግን በኢትዮጵያ የሚሾመው ሊቀ ጳጳሳት ለዘለዓለም የግብፅ ሰው ብቻ እንዲሆን እንጂ ኢትዮጵያዊ አይሆንም ስትል መልስ ሰጠች ለዚህም ማስረጃ ፩ሺ፮፻ ዘመን የቆየ ልማድ መሆኑን ከማስታወሷም በላይ ከቅዱሳን አበው ከሠለስቱ ምእት በጉባዔ ኔቅያ ተጽፎ የተወሰነ ነው ስትል አሳብዋን አስታወቀች ።



www.ethiopianortodox.org

## ስለዘመን ብዛት የጉባኤው ምርመራ

የተቀደሰው ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ከግብፃውያን በኩል የቀረቡትን አሳቦች ከመ ረመረ በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች አስታውቋል ።

የዘመን ብዛት ልማድን ወይም ሥርዓትን ከማሻሻል የሚያግድ አይደለም ፤ ብዙ ዘመን የኖረው የአሪት ሥርዓት እንዳይሻሻል የዘመኑ ብዛት አላገደውም ፤ እንዲሁም ደግሞ በልዩ ልዩ አምልኮት የሚኖሩት አረማውያን አሁን በወንጌል ሲያምኑ የዘመኑ ብዛት ሥርዓት ሆኖ አያግዳቸውም ።

ይህን የመሰለ ብዙ ምሳሌ ይገኛልና ነገሩን ባጭሩ መተው አስፈላጊ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በፈቃዷ ትሠራበት የነበረውን ልማድ አሁን ደግሞ በፈቃዷ ታሻሽለው ዘንድ የሚገባት ሆነ፣ ምክንያቱም የቀድሞው ልማድ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ብርቱ ጉዳት የሚያደርስባት መሆኑ በሚከተሉት ቃላት ስለተገለጸ ነው ።

በኢትዮጵያ ላይ የሚሾሙት ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳት ፩ኛ/የሕዝቡን ቋንቋ የማያውቁና በሕዝቡ ቋንቋ የማይሰበኩ ናቸው ።

፪ኛ/ በቤተክርስቲያኒቱ ወይም ባገሩ ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ ወደሀገራቸው የሚ ሄዱ ናቸው ፤ ከዚህም በቀር ለጠቅላላው አስተዳደር እንቅፋት የሚሆን ምክንያት ን የሚ ያስከትል ጉዳይ መሆኑ አይጠረጠርም ።

ይህንን ሁሉ በማመዛዘን የቆየው ልማድ በሚገባ እንዲለወጥ አስፈለገ ።

## ስለኒቅያ ጥቅስ

የኮፕትን ቤተክርስቲያን የግል ጥቅም ለመመሥረትና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘለዓለም በበታችዋ ሆና እንድትኖር ለማድረግ ምክንያት ሆኖ በየጊዜው የሚጠቀሰውን ቃል ጉባኤው መረመረ ፤ ቃሉም « የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ወገን አለቃ (ሊቀጳጳሳት) አይሹሙ» የሚለው ነው ።

ይህ ጥቅስ በኢትዮጵያውስጥ አዋቂዎች መኖራቸውን እየመሰከረ ሹመቱን ብቻ ይከለክላል ፤ ይኸውም ቃል ለጥቅም ሲታሰብ የተፈጠረ ፤ መሆኑን የሚከተሉት ምክን ያቶች ያስረዳሉ ።

ሀ/ ይህ ቃል በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ስለማይገኝ ፤
ለ/ የክርስትና ሥርዓት የዘርና የወገንን ልዩነት ስለማያደርግ ፤
ሐ/ ኢትዮጵያ ሥርዓተ ክርስትናን የተቀበለችው ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ በመ ሆኑ ከመቀበሏ በፊት የኒቅያ ጉባኤ ይህን ዓይነት ውሳኔ እንደማያወጣባት ለባለአእም ሮው ሁሉ የተገለጠ ስለሆነ ነው ።



በዚህና ይህን በመሰለ ምክንያት ሁሉ ከግብፃውያን የተጠቀሰው ጥቅስ ቀዋሚነት ያለው ሆኖ አልተገመተም ከዚህም በቀር ጉባኤው የተመለከተው ነገር አለ ግብፃውያን የጠቀሱት ይህ ቃል እውነት ነው ቢባል ኖሮ እንኳ የአስተዳደር ጉዳይ ነው እንጂ የሃይ ማኖት ነገር አይደለም የአስተዳደርም ቢሆን እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ከማድረግ የሚከለክል አንዳች ምክንያት አለመኖሩ የታወቀ ነው ። የተቀደሰው ዐቢይ የኢት ዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ይህን ሁሉ ከመረመረ በኋላ ሐምሌ ፯ ፲፱፻፴፰ ዓ ም ያወጣውን የውሳኔ ማስታወቂያ አረጋግጦ ስለተቀበለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳትዋን ከተወላጆችዋ ውስጥ ማግኘት ይገባታል ሲል በአንድ ቃል ተስማምቶ በታል ። ፫ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ተባብረውና ተሳስበው የሚኖሩ ከመሆ ናቸው የተነሣ ቤተ መንግሥት ወደ ኮፕት ጉባኤ መልክተኞቹን ለመላክና እነዚያው የፊተኞቹ ጥያቄዎች እንዲፈጸሙ በበኩሉ እንደገና ለመጠየቅ ማሰቡ በቤተ መንግሥት መልክተኞች አንደበት ለጉባኤው ተነገረ ። የቤተ መንግሥቱ አሳብ የኮፕት ጉባኤ ምናልባት አሳቡን አድሶ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች የሚቀበል ቢሆን ግን ኙነትእንዳያቋርጥ ለማድረግ ሳይሆ ንቢቀር ግን ትሕትናውን እስከሚገባው ደረጃ አድርሶ ለመተው መሆኑን ጉባኤው በትክክል ተረድቶታል ። ጉባኤው በዚህ ነገር አንድ በአንድ ተነጋግሮበታል ከዓባሎቹ ከአራት አንድ እጅ የሚሆኑት የቤተ መንግሥት አሳብ እስ ኪፈጸም ድረስ እንታገሥና ቢሆን ይሆናል ባይሆንም ሥራችንን እንፈጽማለን የሚል ድምፅ ሲሰጡ ሦስት እጅ የሚሆኑት ግን ሥራችንን እንፈጽማለን እንጂ ዳግመኛ ጥያቄ አያስፈልግም ብለው ድምፃቸውን አሰሙ ይሁን እንጂ በጠቅላላው አነጋገር ጉባኤው የመንግሥቱ አሳብ ተቀዋሚ አለመሆኑን ገለጠ ። የጉባኤው ዓባሎች በተከ ታዩ ሰሞን ሱባዔ ለማድረግና የሚገባውን ሥርዓት ለማድረስ ማሰባቸውን ከገለጹ በኋላ ይህ ውሳኔ ፍጻሜ እንዲያገኝ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ያሳሰቡላቸው ዘንድ ለቤተ መንግሥት መልክተኞች ሲያስታውቋቸው እነሱም መልካም ፈቃዳቸው መሆኑን ገለጡ ላቸው ከዚህም በኋላ የጉባዔው ዓባሎች ውሳኔውን አጽድቀውና ፈርመው እንዳበቁ ምዕረገ ጸሎት ተደረጎ ጉባኤው ተነሣ ።

## የብፁዕ ዕጨጌ ማሳሰቢያ

ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ግርማዊ ሆይ !

፩ኛ/ የመንፈሳዊ ዐብይ ጉባኤ በኅዳር ፱ ቀን ከቀትር በኋላ ከ፱ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፱ ሰዓት ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስት ሥላሴ ገዳም ተሰብስቦ በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው የሹመት ሥልጣን ጉዳይ ንግግር ጀመረ ።

፪ኛ/ በዚሁ ወር በ፲፫ኛው ቀን ሐሙስ ተሰብስቦ እስካሁን ድረስ የመንፈሳዊ ጉባኤ ሊቃውንት ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ጋር የተላላኩትንና የተቀባበሉትን መል ክት እንዲሁም ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ጋር በየጊዜው ያደረጉትን ጥያቄና መልስ ሲያጠና ቆየ ።

፫ኛ በዚሁ ወር በ፲፯ኛው ቀን ሰኞ ከጡዋቱ ከ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ፱ ሰዓት ድረስ በተ ደረገው ስብሰባ ከግርማዊነትዎ መልክተኞች ቃል የቤተ መንግሥቱን አሳብና ምኞት ከሰማ በኋላ ከየአውራጃውና ከታላላቅ ገዳማት ለዚሁ ጉዳይ ተመርጠው የመጡት



www.ethiopianortodox.org

መምህራንና ሊቃውንት እያንዳንዳቸው አሳባቸውን እየገለጡ ቃላቸውን ሰጡ ።

ቃላቸውም እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትም ጳጳስም የሚሾመው ከኢትዮጵያ መምህራንና መነኮሳት ውስጥ ብቻ እንዲሆን ብሎ መንፈሳዊ ጉባኤ ፲፱፻፴፯ ዓ ም በሰኔ ፳፩ ቀን ያቀረበው ዋና ጥያቄ የሚገባ መሆኑን ተስማምቶበታል ።

፪ኛ/ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ይህን ጥያቄ ያልተቀበሉት በማይበቃ ምክንያት መሆኑን መላው ጉባኤ ተረድቶታል ።

፫ኛ/ መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ እንዲመረጡ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል ይኸውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለሆነ መንግሥታችን መልክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ጋር በሰላም ለመጨረስ ስለሆነ ይህንኑ በቶሎ ወደ ፍጻሜ እንዲያደርሱላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊነትዎን በጸሎት እየደገፈች ትለምናለች ።

ነገር ግን ግርማዊነትዎ መልክተኞቹን ልኮ ካሁን በፊት በዚሁ ነገር ቤተክህነት የደከመችውን ያህል በነገሩ ደክመውበት ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ፍሬ ያለው ምላሽ ያልተገኘ እንደሆነ አሁን ዐቢይ ጉባኤያችን በቈረጠው ነገር ግርማዊነትዎ የተስማማ እንደሚሆን ባለመጠራጠር እናምናለን ።

ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም አዲስ አበባ ።

ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፡

ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ።

በዚህረገድ ከሁለትዓመታትበኋላ መንሳዊው ትግል የተቀደሰ ፍጻሜ አግኝቶ በ፲፱፻፵ ዓ/ም በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም የተመረጡት የመጀሪያዎቹ ፭ቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በብፁዕ አቡነ ዮሳብ አንብሮተ እድ ተሾሙ ።

## ከጵጵስና እስከ ሊቀ ጵጵስና

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሚገባትን መብት ለማግኘት ወደኮፕት ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ ደብዳቤዎችንና መልእክተኞችን እየላከች በመጠየቋ የተደረገው ክርክር በሰላም መንገድ ከተፈጸመ በኋላ በ፲፱፻፴፰ ዓ ም ሚያዝያ ፲፱ ቀን ከኢትዮጵያ መምሕራን ምርጫ ሲደረግ በተጻፈው ፕሮግራም በ፯ኛው ክፍል በተመለከተው መሠረት ለጊዜው የኢትዮጵያ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ ከኢትዮጵያ መምሕራን ከእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅብአ ጵጵስና ተቀብሎ በበታቹ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም መብት እንዲኖረው ተብሎ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቀደም ሲል የቀረበው ጥያቄ እስኪፈጸም ንግግሩ እንዲቀጥል ሆኖ መቆየቱ ሳይዘነጋ አሁን ለጊዜው የተመረጡት ጳጳሳት ከፓትርያርኩ ይቀበሉ በተባለው ስምምነት የኢትዮጵያ ሊቀ ጵጵስና ሹመት ጊዜውን ሲጠብቅ ቆየ ። ሆኖም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም በማረፋቸው ኢትዮጵያዊት ቤተክርስቲያን በሀዘን ሦስት ወር ከቆየች በኋላ በስምምነቱ መሠረት በአቡነ ቄርሎስ ቦታ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ለመተካት ከስድስቱ ጳጳሳት ውስጥ አንድ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሾም ምርጫ ይደረግ ዘንድ ተወሰነ ።



ይህንንም ታላቅ የሆነ የሊቀ ጳጳሳት መሾም ምርጫ የዘውድ አማካሮች ክቡራን ሚኒስትሮችና ም/ሚኒስትሮች የሕግ መምሪያ፤የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንቶችና አማካሪዎች በኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች፤የሚገኙ አድባራትና ገዳማት አለቆች፤መምሕራንና በከተማ ያሉት ሊቃውንት ታኅሣሥ ፴ ቀን በሊቀ ጳጳሳቱ አዳራሽ ተሰብስበው ባደረጉት ምርጫ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ዕጨጌ ወጳጳስ ዘኢትዮጵያ ከመቶ አምስት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ፲፱፻፵፫ ዓ/ ም ከብፁዕ አቡነ ዮሳብ ዳግማዊ የሊቀ ጵጵስና ሐዐርግ ሲቀበሉ ፤

በዘጠና ስድስት ድምፅ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ስለተመረጡ ከክብር ተከታዮች ጋር ወደ ካይሮ ሄደው የሚመተ ሊቀ ጵጵስናውን ሥርዓተ ቅብዕ ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ በብፁዕ አቡነ ዮሳብ ሥርዓተ ጸሎት ፈጸሙ ።

## የግርማዊ ጃንሆይ መልእክት ፤

«ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለብፁዕ አቡነ ዮሳብ ፪ኛ ፤

ቅዱስቡራኬዎ ይደርሰን ዘንድ እየለመን ሰላምታችንን እናቀርባለን ፤ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሥርዓተ ቅባት ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ካይሮ ላይ እንዲፈጸም የብፁዕነትዎ



www.ethiopianortodox.org

መልካም ፈቃድ መሆኑን የካይሮ ሚኒስትራችን ስላሳወቀን በቤተክርስቲያናችን ሕግ መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ሆነው የተመረጡበትን ተመልክተን እኛም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑ ሹመታቸውን ፈቅደናል ።

ስለዚህ ሥርዓተ ቅባቱ እንዲፈጸምላቸው ልከናቸዋል ።

ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት በፍቅር አስተሳስሮ ለማኖር ሁላችንም የደከምንበት ጉዳይ በዘመነ መንግሥታችንና ብጹዕነትዎ በመንበረ ማርቆስ በተቀመጡበት ዘመን ፍጻሜ በማግኘቱ ይኸን ዕድል ለሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና እያቀረብን የተሰማንን ታላቅ ደስታ ለብፁዕነትዎ እንገልጻለን ።

ለብጹዕነትዎ ረጅም ዕድሜ መልካም ጤና ልዑል እግዚአብሔር እንዲሰጥ ከልባችን እንመኛለን።ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ/ም በነገሥን በ፳ኛው ዓመት በአዲስ አበባ ቤተመንግሥታችን ተጻፈ ።

ቀ ኃይለ ሥላሴ ን ነ ዘኢትዮጵያ ።

# ከጵጵስና እስከ ፓትርያርክነት

## ጠቅላላ መግለጫ ፤

ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት ነጻነቷን ጠብቃና ክብሯን ሳታስነካ የቆየች ሀገር ለመሆኗ ታሪኳ ይመሰክራል ። በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋዊ ነጻነቷ ይኑር እንጂ በመንፈሳዊ በኩል ለረጅም ጊዜ ሲመተ ጵጵስናን ለማግኘት ዕድል ተነፍጓት ቆይታለች ።

እንዲያውም ቀደም ብሎን የኢትዮጵያን የክርስትና አመሠራረት የተመለከትን እንደሆነ የጵጵስናውም እርምጃ ከእዚሁ ጋር አብሮ ጐን ለጐን ታሪክን የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ይኸውም ኢትዮጵያየክርስትና እምነትን የተቀበለችው በ፫፻፴ ዓ/ም አካባቢ ሲሆን ክርስትናን ኢትዮጵያ እንድትቀበል ባደረጉት በአብርሃና በአጽብሃ ነገሥታተ አክሱም ፈቃድና ትዕዛዝ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ሔዶ ጳጳስ እንዲያመጣ ተደረገ ወዲያው ወደ እስክንድርያ ሒዶ ያን ጊዜ የእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ ከነበረው ከአቡነ አትናቴዎስ ዘንድ ቀርቦ ኢትዮጵያውያን ክርስትናን ለመቀበል የሚወዱ መሆናቸውን አስረድቶ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲልክ ቢጠይቀው ከአንተ የተሻለ ጳጳስ አናገኝም አንተ የሕዝቡን ባህል፣ቋንቋና ሥነሥርዓት ስለምታውቅ ጳጳስነቱን ይዘህ ሒድ ስለአለው የጵጵስና ሹመት ተሰጥቶት «አባ ሰላማ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ»በሚል ሥያሜ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ ። ኢትዮጵያውያንም አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ብለው ጠሩት ይህ ከተፈጸመ ዛሬ ፩ሺ፮፻፲፫ አመት ሆነው ።

ከእዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ራሷን መወከል ሳትችል እስክንድርያ የበላይነቱን ይዛ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስትመራ ቆየች ።

በጠቅላላው መንፈሳዊውን የበላይነት ይዛ የምትመራው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እንጅ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለእዚህ ከፍተኛ የመንፈሳዊ ክብር የተለዩ መንበር አልነበራትም ።



ቢሆንም ከፍተኛና የዲፕሎማሲ አመራራቸውን በረቀቀ ጥበብና አስተዋይነት የሚመሩት የኢት ን ነ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ኢትዮጵያ የመንፈሳዊ ነጻነት ክብሯ መጓደሉን ቢያውቁም ጊዜውን አስጠብቀው የፈጣሪያቸውን ኃይል ድጋፍ አድርገው ኢትዮጵያ ከ፩ሺ፮፻ ዓመት በላይ ያላገኘችውን ክብር ለማስገኘት ትግላቸውን በመ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በሊቀ ጵጵስና መዐርግ ጊዜ፤

ቀጠል የኢትዮጵያ ጳጳሳት እንዲሾሙ በማድረግ ያደረጉት ጥረት በ፲፱፻፵ ዓ ም ድልን ስላገኘ በጃንሆይ ጥረትና የድፕሎማሲ ችሎታ አምስት ኢትዮጵያን ሊቃነ ጳጳሳት ለመሾምቻሉ፤ይህለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛና የመጀመሪያው መንፈሳዊ ምሥራች ነበር ።



www.ethiopianortodox.org

ኢትዮጵያ ይህንን መንፈሳዊ ሥልጣን ይገኘችው ግርማዊ ን ነ ቀ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፲፮ኛው ዓመት ኢትዮጵያ ክርስትናን ተቀብላ የጳጳሳትን መሾም ካጣች ከ፩ሺ፮፻፲ ዓመታት በኋላነበር፣ በአጭር ጊዜ የረጅም ዘመናት ችግር መወጣትና መንፈሳዊ ክብርን ማስገኘት ይህ ራሱ ንጉሠ ነገሥቱን ለእዚህ ታላቅ የብቃት ሥራ ቀደም አድርጎ ልዑል እግዚአብሔር የመረጣቸው መሆኑን ይመሰክራል። ለሥራ የሚመረጥ፣ለሥራ የሚሾም፡ለሥራ የሚመራ፤የሚገኘው እግዚአብሔር በወደደው ጊዜና በመረጠው ሰው አማካይነት ነው።ክቡር ዳዊት የእግዚአብሔር መመስገኛና መመለኪያ የሚሆን ቤተ መቅደስ ለመሥራት በተነሣ ጊዜ «አንተ ቤት የምትሠራልኝ አይደለህም ከወገብህ የሚወጣው ልጅህ እንጅ እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል » ብሎት ልጁሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠራ መጽነገ ቀዳ ምዕ ፰ ቁጥር ፲፰ የአለፉት ነገሥታት ይህን ክብር ያዩ ዘንድ ይፈጽሙም ዘንድ ፈለጉ ግን አላገኙም ። ይህን ታላቅ መንፈሳዊ ክብር ለማየትና ለመፈጸም ከእግዚአብሔር የታዘዙና የተመረጡት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመሆናቸው ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን የክብር ደረጃ ሊያስገኙ ችለዋል ። ዛሬ ይህንን የሊቀ ጵጵስና ክብር የኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ከተቀበለች ፳፭ ዓመት ሆነ ክብሩን በታላቅ ሥነሥርዓት የምናከብረው በእዚያን ጊዜ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የሾመቻቸውን የአምስቱን ጳጳሳት የብር ኢዮቤልዩ ነው ።

በእዚያን ጊዜ በእስክንድርያው መንበረማርቆስ አንብሮተ እድ ሥልጣን የተሾሙት

፩ኛ/ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ፤

፪ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ፤

፫ኛ/ መምህር ገሪማ፤ (አቡነ ሚካኤል )፤

፬ኛ/ መምህር ዘፈረ ብርሃን ፤( አቡነ ያዕቆብ)

፭ኛ/ መምህርጌታሁን (አቡነ ጢሞቴዎስ)ነበሩ ስለጵጵስናውሥርዓተሢመት ቀደም ሲል ብዙ ችግርና ክርክር ቢደረግበትም ቅሉ እነዚህ ብፁዓን አበው የሔዱበት ተልእኮ በሚገባ ተከናውኖ ስለተፈጸመ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፵ ዓ ም በዕለተ ዕሁድ በበትረ ካና ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ የመንፈሳዊ በዓል ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ በእዚያን ጊዜ የእስክንድርያ ፓትርያርክ በነበሩት በብፁዕ በአቡነ ዮሳብ ጸሎት መዓርገ ጵጵስና ተሰጣቸው ።

ይህን ከፍተኛ መንፈሳዊ ድል የተፈጸመበትን በግርማዊነታቸው ታላቅ አስተዋይነትናከፍተኛ ተጋድሎ የጵጵስና ማዕርግ ኢትዮጵያ ውያን አባቶች የተቀበሉበትን ሃያ አምስተኛ የብር ኢዮቤልዩ በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት እናከብረዋለን፣ ።

ቤተ ክርስቲያናችን በእዚህ ደረጃ ብቻ ተወስና እንድትቀር አልተደረገም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሁንም ኢትዮጵያ ራሷን በራሷሥልጣን የምታሳውቅበት ደረጃ እንዲኖራት ፕሮግራምን ጠብቀው ጥረታቸውን ስላላቋረጡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የሊቀ ጳጳሳት ሥልጣን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ አግኝተው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙች ጳጳሳትን የመሾም ሥልጣንን አግኝታለች ።

ይልቁንም የጃንሆይ ጥረት ፍሬን አግኝቶ በግርማዊነታቸው ብርቱ ትግልና ድካም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን የፓትርያርክነት ሥልጣን





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ጊዜ



www.ethiopianortodox.org

ልታገኝ ችላለች፡፡ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ራሳቸው ሰኔ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ ም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ካይሮ ከተማ ውስጥ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ስድሳዊ የእስክንድርያ ፓፓና ፓትርያርክ ሥርዓተ ጸሎት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ሲቀዳጁ በእዚህ መንፈሳዊ በዓል ላይ ተገኝተዋል ። ይህም ጃንሆይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደግና ለከፍተኛው ክብር ብቁዕ ለማድረግ ያስመሰከሩበትና ጃንሆይ በመንፈሳዊ ነጹነትም ባለድል መሆናቸውን ያረጋግጣል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ፲፪ ዓመታት ያህል በፓትርያርክነት ሥልጣን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ከቆዩ በኋላ ከእዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

ከእዚህ በኋላ በአቡነ ባስልዮስ ወንበር የተተኩትን የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በገዛ ራሷ ሥልጣን ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪኳ ውስጥ መዝግባ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ፓትርያርክ አድርጋ ሾመች ።

በእኒህም ታላቅ መንፈሳዊ አባት የፓትርያርክነት ሹመት ግርማዊነታቸው ለረጅም ጊዜ ያደረጉት መንፈሳዊ ትግልና ጥረት ፍሬ አፍርቶ በመንበረ ፀባዖት ካቴድራል ውስጥ በኢትዮጵያ በነገሥታቷ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን ድል በዓይናቸው ተመልክተዋል ።

ይህንን መንፈሳዊ ድል የተመለከትን ኢትዮጵያን ሁሉ ብፁዓን ነን ።

## ታሪክና ሥራ ፤

ቀደም ባለው ዘመን የተፈጸመውና ለጊዜው በዜና መልክ ተመዝግቦ የኖረው ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ዕለታዊ ተግባር ሁሉ ከዘመን በኋላ ለተነሣው ትውልድ ከዘመን በፊት የነበረው የትውልድ ታሪክ ሆኖ ይቀርባል ። በዚህ ረገድ ሥራ ታሪክ ነው ፤ ታሪክም ሥራ ነው ፤ ሥራ ከሌለ ታሪክ የለም ፤ ታሪክ ም ከሌለ አገርና ወገን አለ ተብሎ አይወራም በዘመናት ብዛት የተሸፈነው የሀገርና የወገን ሕልውና ለደሐራዊው ትውልድ ጉልሕ ሆኖ የሚታየው በታሪክ መስተዋትነት ነው ፤ ታሪክ እንደመስታወት ሆኖ የኋላውንና የፊቱን የተፈጥሮ ግዴታ ባያሳይ ኑሮ ሕይወት ሁሉ መሕኑ(ውሉ)የጠፋበት ድርና ማግ ሆኖ ይቀር እንደነበር አእምሮ ያምንበታል ።

እነሆ ከአራት መቶ ዘመናት በፊት የወንጌል ማዕድ የተዘረጋላት ፤ ከሦስት ሺህ ዘመናት በላይ የነጻነት ብርሃንየበራለት፤ በጥንታዊውክርስቲያንነቷ «ሀገረአምላክ ፤ የክርስትና ደሴት» ተብላ የምትጠራው ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ከፖለቲካ ሰውነታቸው ጋር «የሃይማኖት ጠበቃ» ተብለው በሚጠሩት በዕድለኛው ንጉሥ ነገሥት በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ክርስቲያናዊ ጥረት በቅዱሳን አበው ጸሎት ሙሉ መንፈሳዊ ነጻነቷን ከተጐናጸፈች አንድ ማዕከላዊ የሥራ ዘመን አሳልፋለች፤ይኸውም ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሚከበረው ፳፭ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ጵጵስና የብር ኢዮቤልዩ ነው ።

ጥንታዊቷ ፤ ኦርቶዶክሳዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእዚህ የብር ኢዮቤልዩ ዘመን ውስጥ የብዙ መሲሐውያት ሥልጣናት ባለቤት ሆናለች፤ከዕጨጌነት እስከ ጵጵስና



ቤተ መጻሕፍት

ጵጵስና እስከ ሊቀ ጵጵስና ከሊቀጵጵስና፤እስከፍጹሙ የፓትርያርክነት ደረጃ ደርሳለች ምስጋና ለእግዚአብሔር ይግባውና በብዙ መንፈሳዊ ትግል መሰላልነት ወደ እዚህ ከፍተኛ ደረጃ ከተረማመደች በኋላ በራሷ ቅዱስ አንብሮተ እድ ብዞች ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትነትን በመሾም መሲሐዊ ሥልጣኗን አበርክታለች ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቀዳጀችው ሙሉ መንፈሳዊ ነጻነት በአምላካዊተአምር እንዲሁያለድካም የተገኘ ነጻነትአይደለም።የኢትዮጵያንቤተ ክርስቲያን ለመጨቆን በተወሰደው እርምጃ «የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸውአይሹሙ» በሚለው የፈጠራ ጥቅስ ከዛሬ ፵ ዓመት በፊት ብዙ ኢትዮጵያዊውያን ሊቃውንት ብዙ ጊዜ ተከራክረውበታል ፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን አባቶች ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ በመመላለስ ጉልበታቸውን ሰውተውበታል ።

ከብዙ ትግል በኋላ የተገኘው የዚህ መንፈሳዊ ጸጋ የክብሩም የድካሙም ተካፋዮች ከኢትዮጵያውያን አባቶች ውስጥ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው ፤ እነሱም በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና ዛሬ በመንበራቸው የተተኩት ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ናቸው ። የእነዚህ የሁለቱ አበው ትሑት ሰውነት ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ስለተከራከረና የመንፈሳዊ ክብር ተቀባይ ስለሆነ ሁለቱ አባቶች እውነትም ብፁዐን ናቸው ።

በመንፈሳዊው ጉዳይ የባዕድ እጅና አንደበት ትመለከት የነበረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከወገኖቿ ጳጳሳትን እየሾመች ከሀገር ውስጥ አልፋ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ታስተምራለች የልዩ ልዩ ክፍለ ዓለማት ነገዶች ባህሏንና ሃይማኖቷን በመውደድ «ታስተምረን እናምንበታለን» በማለት የክርስትና ድምፃቸውን በማሰማት ላይ ናቸው። ይህ እንግዲህ ሊያስደስትም ሊያሳስብም የሚችል ከድልበኋላ የተገኘ መንፈሳዊ ደስታና ፈተና መሆኑን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልትገነዘበው ይገባታል ።

የአባቶቻችንን የረጅም ጊዜ መንፈሳዊ ትግል በቀላሉ ባንገምተውም በአዋቂዎች ዘንድ ማግኘት ቀላል ነው በተገኘው በሚገባ መጠቀም ግን እጅግ በጣም ከባድ ነው ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመጨረሻው መንፈሳዊ ግብ ደርሳለች በሥልጣን እረገድ የምትፈልገው ምንም ነገር የለም ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚፈለገው ከዘመናዊው ሥልጣኔ ጋር ጐን ለጐን የተሰለፈ ሐዋርያዊ ተግባር ነው ይህ ካልሆነ «ጊዜና ውሃ ሙላት ሰውን ስለማይጠብቅ » አልፏት ይሄዳል ጊዜውም ካለፉት የታሪክ ቅርስነቷን እንደያዘች መታሰቢያ ሆና መቅረቷ አያጠራጥርም ።

ይህ ፳፭ኛው ዓመት የብር ኢዮቤልዩ መንፈሳዊው ነፃነት ቀስ በቀስ የተገኘበት ወይም ሌሎች ማለት ያለፉት ኢትዮጵያውያን አባቶች የደከሙበት የታሪክ ዘመን ስለሆነ መታሰቢያነቱ እንዳለ ሆኖ ባረጀ ጊዜ የሚደግፈው ሌላ ታሪክ መውለድ አለበት፤ይኸውም ታሪክ ሥራ ነው። ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ታሪክ ትውልድን የሚያንጓውና የሚያኮራው ደሐራዊ ታሪክ ከቀዳማዊ ታሪክ ሲወለድ ነው ፤ ታሪክ ሁሉ የጥንታዊው ትውልድ ውጤት መሆኑ ባይካድም ዘመናዊ ሥራ ካልተጨመረበት ፃማ ከናፍር ነው ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሐዋርያዊው የሥራ እርምጃዋ መንፈሳዊ ነጻነቷን ለማግኘት ካደረገችው የረጅም ዘመናት ትግልና ጥረት የሚበልጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርባታል ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምክንያት የላትም



www.ethiopianortodox.org

ባለፉት ዘመናት የሊቃውንቷ ጉባኤና ውሳኔ እንደሚያስረዳን በመብት፣ በቋንቋ ታመ ካኝ ነበር ዛሬ ግን መብቱ የግሏ ፓትርያርኩ የራስዋ ነው ቋንቋውም ቋንቋዋ ስለሆነ በእ ርስዋናበሕዝቧ መካከል ያለው ያለመግባባት ችግር ተወግድዋል ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ኃላፊነቷ ከብድዋልና ካለፈው የበለጠች ሆና መገኘት አለባት ።

ያለፈውን ጊዜ የብር ኢዮቤልዩ የታሪክ ዘመን እንበለው የሚቀጥለው የወርቅ ኢዮቤልዩ ግን የሥራ ዘመን መሆን ይገባዋል ፤ ክርስቲያናዊ ፍቅር በቀዘቀዘበት ፣ ሰላምና የመንፈስ እረፍት በታጣበት በጠቅላላው መንፈሳዊው ሕይወት ባለጠበት ዘመናዊ ሥልጣኔበገነነበት፣ጊዜያዊፍልስፍና በተስፋፋበትበዚህየመሸጋገሪያክፍለዘመን ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያዊ ትውልድ ፤ ለአፍሪካ ሕዝብም ጭምር ታላቅ ኃላፊነት አለባት ፤ ምክንያቱም እንደተገለጸው ሁሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ የክር ስትና ደሴት ናትና ።

ዛሬ ያሉት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስቆጶሳት የ፲፬ ጠ/ግዛት ተወላጆች ስለሆኑ እንኳን በዘመናዊ መገናኛ በእግራቸውም ቢሆን በኢትዮጵያ ጠረፍ በመዘዋወር ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ለመፈጸም የሚያስጋቸው ጉዳይና የሚገጥማቸው ችግር የለም ፤ ብቻ የሚመረጡት ሐዋርያት የሥጋ ሳይሆኑ የመንፈስ ሐዋርያት መሆን አለባቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትሾማቸውን ሐዋርያትና ሁሉ ብዛ ታቸውን ሳይሆን ዓይነታቸውን መመልከት አለባት የስም ሐዋርያትና የግብር ሐዋር ያት አሉና። ለማይሠራ ብዛት አይጠቅምም ፈረንጆች «ወጠ ሠሪ ሲበዛ ጐመንይጠነዛ» ብለው ይናገራሉ ። ሐዋርያው ያዕቆብም መምህራን አይብዙ ያለው የማይሠሩትን እንጅ የወንጌል ተቀዋሚ ሆኖ አይደለም ።

መንፈሳዊ ሹመት ሥጋዊ ክብርን አይሻም ሥጋዊ ክብርን የሚፈልግ መንፈሳዊ ሰው ካለ እሱ መንፈሳዊ አይደለም ይህም ማለት በአሁኑ ጊዜ ያሉት የሐዋርያት ተከታዮች ሰማያዊውን ፎመሻት የዚህን ዓለም ክብር ሳይሹ ወንጌልን ያስተምሩ ማለት ነው ምክንያቱም ወንጌል የምግባርና የትሩፋት፤የስብከትና የስደት እንጅ የሹመትና የሺልማት የመብልና የድሎት አይደለችምና ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክበተናገሩትቃል «በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ነገሮች ያስፈልጓታል እነሱም ትጋትና ትብብር ናቸው» ብለው እንደተናገሩት ለሁሉም መንፈሳዊ ትጋትና ትብብር ያስፈል ልጋል ሃያ አምስተኛውን ዓመት የመንፈሳዊ ድል የብር ኢዮቤልዩ ለማክበር እንደ በቃን ሁሉ በሚቀጥለው ዘመን የምንመኘውን የሥራ ኢዮቤልዩ ለማክበር እንድን በቃ የኢትዮጵያው ያን ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ መንፈሳዊ ምኞት ሊሆን ይገባዋል ።



www.ethiopianortodox.org